የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሠራር እና ስነ ምግባር

## *መመሪያ*

## ቁጥር 5/2012 ዓ.ም

*መግቢያ*

በምርጫ ሂደት የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች መኖር ነፃ እና ገለልተኛ ምርጫ እንዲኖር በማድረግ ያለውን ሚና በመገንዘብ፤

የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎችን ማንነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓቱን እና ተግባርና ሃላፊነታቸውን እንዲሁም መብቶቻቸውን በግልፅ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአገር ውስጥ በምርጫ ታዛቢነት የሚሰማሩ ድርጅቶች እና ተወካዮቻቸው ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነምግባር መርሆዎችን ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 114 እስከ 117 እና በቦርዱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር1133/2011 አንቀፅ 7 ንኡስ አንቀፅ (7) እና አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ (1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀፅ 1.** አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሠራር እና ስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር …/2012 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤ 1) "የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ" ማለት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ከቦርዱ ፍቃድ አግኝቶ በተወካዩ አማካኝነት ምርጫን የሚታዘብ በህግ የተመዘገበ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ የሀገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ሲሆን የሙያ ማኅበራትን፤ የብዙኃን ማህበራትን እና ሌሎች የሀገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኅብረቶችን ይጨምራል።

2) "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ.ም ነው።

3) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው። 4) "ወኪል" ማለት በቦርዱ የታዛቢነት ፈቃድ ያገኘ ድርጅት ምርጫውን እንዲታዘብለት የሚመድበውና በቦርዱ ተቀባይነት አግኝቶ ምርጫን እንዲታዘብ መታወቂያ የተሰጠው ሰው ነው። 5) "አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት" ወይም "ድርጅት" ማለት ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሰረት የመንግስት አካል ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ፣ እና ህጋዊ አላማን ለማሳካት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ሲሆን፣ የሙያ ማህበራት፣ የብዙሃን ማህበራት እና የድርጅቶች ህብረቶችን የሚጨምር ነው።

6) “ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት” ማለት በማንኛውም መደበኛ ሁኔታ ይደርሳሉ ተብሎ ያልተገመቱ እና ያልተጠበቁ፣ ከአመልካቿ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት የሚደርሱ እና እንዳይደርሱ መከላከል ወይም ማስቆም የማይቻሉ ክስተቶች ናቸው።

**7)** “የጥቅም ግጭት” ማለት በታዛቢዋ እና በእጩ ተወዳዳሪዋ መካካል የሚኖር ወደላይ ወይም ወደታች የሚቆጠር ዝምድና፣ የገንዘብ ጥቅም፣ ግጭት እና ቦርዱ እንደየአግባብነቱ የጥቅም ግጭት መንስኤ ናቸው ብሎ የሚወስናቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች ናቸው።

8) የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1133/2011ዓ.ም እና በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ.ም ያሉ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ።

አንቀፅ **3.** <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በሴት ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል።

አንቀፅ **4.** <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ምርጫ፣ በአካባቢ ምርጫ፣ በማሟያ ምርጫ፣ በድጋሚ ምርጫ ወይም በህገ መንግሥቱ እና በአዋጁ መሠረት የሚካሄድ ህዝበ ውሳኔ ላይ ለመታዘብ ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጣቸው የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

## ክፍል ሁለት
## ስለታዛቢነት ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብና ስለፈቃድ አሰጣጥ

### አንቀፅ 5. የታዛቢነት ጥያቄ ስለማቅረብ

1) ምርጫን ለመታዘብ የሚፈልግ ማንኛውም አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ቦርዱ ለዚሁ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የሚጠየቁ መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚገልጹ ማስረጃዎችን በማያያዝ ለቦርዱ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። 2) ማንኛውም ድርጅት ከቦርዱ ፈቃድ ሳያገኝ በታዛቢነት ሊሰማራ አይችልም።

### አንቀፅ 6. የታዛቢነት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለበት መመዘኛ

**1.** ማንኛውም የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፡

ሀ) ሕጋዊ ሰውነት ያለው፣

ለ) ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ የሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ እና የመንግስት አካል ያልሆነ፣

ሐ) የቦርድ አባላቱና መሪዎቹ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑ፣

መ) የሚያሰማራቸው ታዛቢዎች ምርጫን በገለልተኝነት ለመታዘብ የሚችሉ እንዲሁም ድርጅቱ የማስፈፀም አቅም ያለው፣ መሆን አለበት።

**2.** ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ ድርጅት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህብረት ከሆነ ሁሉም አባል ድርጅቶች በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ግዴታዎች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።



አንቀፅ **7.** <u>ከታዛቢነት ማመልከቻ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት ከሚቀርብ የምርጫ ታዛቢነት ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች በአባሪነት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

ሀ) ፈቃድ ጠያቂው ድርጅት ስልጣን ካለው መንግስታዊ ተቋም የተሰጠውና በአገር በቀል የሲቪል ማህበርነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ) ድርጅቱ በቦርዱ የተዘጋጀውን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጽ በተቋሙ ማህተምና የበላይ ኃላፊ ፊርማ የተረጋገጠ ሰነድ፣

ሐ) ቦርዱ ለዚሁ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ የሚሞላ ሆኖ ድርጅቱ በምርጫ ታዛቢነት የሚያሰማራቸው ተወካዮች በቦርዱ የተዘጋጀውን የስነምግባር ደንብ አክብረው ለመንቀሳቀስ የተስማሙ ስለመሆኑ በእያንዳንዱ ተወካይ ፊርማ የተረጋገጠ ሰነድ፣

መ) በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሐ) ከተመለከተው ሰነድ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የተወካይዋ ሙሉ ስም እና የወከለችውን ድርጅት ስም በጀርባው የያዘ ተወካይዋ በቅርብ ጊዜ የተነሳችው ሁለት የፓስፖርት መጠን ጉርድ ፎቶዎች፣

ሠ) የተወካይዋን ማንነት የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ኮፒ።

<u>አንቀጽ **8.** በምርጫ ታዛቢ ድርጅት ስለሚቀርቡ ወኪሎች</u>

1) በምርጫ ታዛቢ ድርጅት የምትሰማራ ተወካይ፦

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላት፣

ለ) እድሜዋ 21 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

ሐ) የመምረጥ እና የመመረጥ መብቷ በሕግ ያልተገደበ፣

መ) የታወቀ ብልሹ ስነ-ምግባር የሌላት፣

ሠ) በእጩ ተወዳዳሪነት ያልተመዘገበች፣

ረ) ቀደም ሲል በምርጫ ታዛቢ ተወካይነት ተሰማርታ በቦርዱ ያልታገደች መሆን አለባት።



2) ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ምርጫን የሚታዘበው በቦርዱ ተመዝግባ ፈቃድ እና

መታወቂያ ወረቀት በተሰጣት ተወካዩ አማካይነት ነው።

3) የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ቀደም ሲል ለቦርዱ ያሳወቃትን ተወካይ ለመቀየር ከፈለገ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ስለተወካዮች የተነገሩትን በማሟላት መቀየር ይችላል።

4) ማንኛውም ምርጫ እንዲታዘብ ፈቃድ የተሰጠው የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ለተወካዮቹ ስለ ምርጫ ሂደቶች ፣ ስለ ምርጫ ህጐች እና አሠራሮች እና ስለዚህ የስነ-ምግባር መመሪያ ድንጋጌዎች የተሟላ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ መቻል አለበት።

አንቀፅ **9.** <u>ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>

1) ቦርዱ የአገር ውስጥ የታዛቢነት ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት እና ተወካዮቹ በምርጫ ሕጉ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን መስፈርቶች እና ግዴታዎች ያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ፣ የድርጅቱን የማስፈጸም አቅም በማገናዘብ እና የምርጫ ሕጎቹንና ይህንን መመሪያ ለማክበር መስማማቷን የድርጅቱን ዋና ሃላፊ ወይም ተወካይዋን በማስፈረም የታዛቢነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

2) ቦርዱ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መመዘኛዎችንና መስፈርቶችን ለማያሟላ ድርጅት የታዛቢነት ፈቃድ አይሰጥም፤ ይህንን ውሳኔውንም ለአመልካቹ ድርጅት በ30 ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ያሳውቀዋል።

3) ማንኛውም በቦርዱ የተሰጠ የታዛቢነት ፈቃድ የሚያገለግለው በአንድ ወቅት በሚካሄድ ምርጫ

ሆኖየምርጫው ውጤት በቦርዱ በይፋ እስከሚገለፅበት ዕለት ብቻ ነው።





**አንቀፅ 10.** <u>የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት</u>

1) ቦርዱ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ የሰጠው ድርጅት በመመሪያው መሠረት ላቀረባቸው ተወካዮች ለእያንዳንዳቸው የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ ይሰጣል።

2) ማንኛውም በቦርዱ የተሰጠ የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ የሚያገለግለው በአንድ ወቅት የሚካሄድ የምርጫ ውጤት በየምርጫ ጣቢያውና በየምርጫ ክልሉ እስከሚገለፅበት ዕለት ብቻ ነው።

3) ቦርዱ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ተወካዮች የሚያዘጋጀው የመታወቂያ ካርድ የሚከተሉትን የያዘ ይሆናል።

ሀ) የቦርዱን ሎጎ /አርማ/፣

ለ) የወከለችውን ድርጅት ስም እና የተወካይዋን ፎቶግራፍ፣

ሐ) የተወካይዋን ሙሉ ስም፣

መ) የቦርዱ ማህተም፣

ሠ) መታወቂያው የሚፀናበት ጊዜ፣

ረ) የመታወቂያ ቁጥር፣

ሰ) ፈቃዱን የሠጠችው ኃላፊ ስም እና ፊርማ፣ እና

ሸ) የባለመታወቂያዋ ፊርማ

4) የታዛቢነት ፈቃድ ያገኘ ድርጅት ተወካይዋን ከቀየረ ወይም ድርጅቱ ወይም ተወካይዋ የመታዘብ

ሥራዋን ካቋረጠች የታዛቢነት መታወቂያዋን ተረክቦ ለቦርዱ መመለስ አለበት።



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

## ክፍል ሶስት

## የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ መብትና ግዴታ

**አንቀፅ 11.** የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢ መብት

ከቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት የምስክር ወረቀት ያገኘ ድርጅት ተወካይ፤

ሀ) በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት ማለትም የመራጮች ምዝገባን፣ የእጩዎች ምዝገባንና የምርጫ ቅስቀሳን እንደዚሁም የድምፅ አሰጣጥን፣ የቆጠራ ሂደትን እና የውጤት አገላለጽን የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቃ የማግኘት መብት፣

ለ) የምርጫ ሰነዶችን የመመልከት፤ የድምጽ አሰጣጥ እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን የመታዘብ፣ ሐ) በምርጫው ሂደት የታዘበቸውን ወይም ያጋጠማትን ጉድለቶች ለቦርዱ ወይም በየደረጃው ላሉ የቦርዱ ጽ/ቤቶች የማቅረብ፣

መ) ከማንኛውም መንግስታዊም ሆነ ከማናቸውም ሌላ ተቋም ወይም ሰው ተፅእኖ ነፃ የመሆን፣ ሠ) ምልከታዋን፣ ትዝብቷን ወይም ግኝቷን እና የደረሰችበትን ድምዳሜ አስመልክቶ ለህዝብ ይፋ መግለጫ የመስጠት፣

ረ) ከቦርዱና ከአካባቢ ባለስልጣናት እንደዚሁም በየደረጃው ከሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ትብብር የማግኘት፣ መብት አላት።

**አንቀጽ 12.** የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢ ግዴታ

1) ከቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት የምስክር ወረቀት ያገኘች የምርጫ ታዛቢ:-

ሀ) የታዛቢነት መታወቂያዋን በግልጽ ማንጠልጠል፣

ለ) የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጧትን መመሪያ ማክበር፣

ሐ) የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደናቅፍ ተግባር መቆጠብ፣





መ) ቦርዱ ያወጣውን የስነ-ምግባር መመሪያ ማክበር፣
ሠ) ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅታ ለቦርዱ የማቅረብ፣ግዴታ አለባት።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሠ) የተመለከተው ሪፖርት በሚከተለው አኳኋን መቅረብ አለበት፤

ሀ) ማንኛውም ተወካይ ለወከለችው ድርጅት ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅታ የተሰማራችበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት በተገለፀ ከ7 እስከ 10 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለባት።

ለ) ማንኛውም የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ስለታዘበው የምርጫ እንቅስቃሴ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ቦርዱ የምርጫውን ውጤት ይፋ ካደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት። የሪፖርቱ ይዘትም፦

1. ድርጅቱ በምርጫ ታዛቢነት ሥራው የሸፈነው ክልል፣ ዞን፣ የምርጫ ክልል ወይም ምርጫ ጣቢያ ብዛት እና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውን፣

2. በእያንዳንዱ የምርጫ እንቅስቃሴ ሂደት፣ በምርጫ ዝግጅት፣ በመራጮች ምዝገባ፣ በእጩዎች ምዝገባ፣ በምርጫ ዘመቻ፣ በድምፅ አሰጣጥ፣ በድምፅ ቆጠራ እና በውጤት አገላለፅ ላይ የታዘባቸውን ሁኔታዎችና የተጠቀመባቸው መረጃዎች፣

3. የትዝብት ሪፖርቱ በምርጫ ሂደቱ ያለውን የዖታ ተዋፅኦ ዝርዝር የሚያሳይ መሆን አለበት።

አንቀፅ **13.** <u>ምርጫን ለመታዘብ ስለሚያስፈልጉ ወጪዎችና ስለስልጠና</u>

1) ማንኛዋም ምርጫን የምትታዘብ ተወካይ ለዚህ ሥራ የሚያስፈልገውን ወጪ የምትሸፍነው በራሷ ወይም በወከላት ድርጅት ነው። የቦርዱን፣ የማንኛውም የፖሊቲካ ፓርቲን ወይም፣ የማንኛውም የመንግስት ተቋም ተሽከርካሪ ወይም ሌላ ሀብት መጠቀም የተከለከለ ነው።



2) ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ተቋም የወከላቸው ታዛቢዎች ተግባራቸውን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ከመጀመራቸው በፊት፦

ሀ) ስለ ምርጫ ሂደቶች፣

ለ) በምርጫ ህጎች እና አሠራሮች እንዲሁም

ሐ) በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ላይ የተሟላ ስልጠና እንዲያገኙ እና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት።

## ክፍል አራት

## የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነምግባር ድንጋጌዎች

### አንቀፅ **14.** ህግን ስለማክበር

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ወኪሏ፦

ሀ) አዋጁን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንደዚሁም ሌሎች ተዛማጅ ህጎችን ማክበር፣ ለ) በቦርዱ የተሰጣትን የመታወቂያ ካርድ በግልጽ በማንጠልጠል መንቀሳቀስ እና በሚመለከተው አካል ስትጠየቅ ማንነቷን የሚያረጋግጥ ፓስፖርት ወይም መታወቂያ፣ማሳየት አለባት።

### አንቀጽ **15.** የምርጫ አስፈፃሚዎችን ስልጣን ማክበር

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ወኪሏ፦

ሀ) የቦርዱን እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ የፀጥታና ደህንነት እንደዚሁም የሌሎች የመንግስት አካላት የሚሰጧትን ህጋዊ ትዕዛዝና መመሪያ መቀበልና ማክበር፣





ለ) ከምርጫ አስፈፃሚዎች እንደዚሁም ከሌሎች ታዛቢዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት አለባት።

## አንቀጽ 16. <u>ምክር ስላለመስጠት</u>

ማንኛውም ፍቃድ የተሰጠው የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት እና ተወካይዋ፤ ሀ) ለምርጫ አስፈፃሚዎች ከኃላፊነታቸው ጋር የተያያዘ መመሪያ ወይም ምክር መስጠት የለባትም፣

ለ) የሚመለከቷቸውን የጎሉ ስህተቶችን ለምርጫ አስፈፃሚዎች ሪፖርት ከማድረግ ውጭ ምክር በመስጠት ችግሮችን ለመፍታት አለመንቀሳቀስ፣

ሐ) የአፈታት ሂደቱን ከመታዘብ ውጭ የውይይቱ አካል በመሆን በቅሬታ /አቤቱታ/ በመፍታት ሂደት ውስጥ መሳተፍ፣ የለባትም።

## አንቀፅ 17. <u>ገለልተኛ ስለመሆን</u>

ፈቃድ የተሰጠው የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪሏ፦

ሀ) ተግባራቷን ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን ማከናወን፤ ከማንኛውም አካል ጋር በማንኛውም ሁኔታ

ገለልተኝነቷን ከሚጎዳ ወይም ወገንተኝነትን ከሚያሳይ እንቅስቃሴ መቆጠብ፣ ለ) የፖለቲካ ድርጅቶችን ወይም እጩን ወገንተኝነት ሊገልፅ ከሚችል በነዚህ አካላት ወይም ሰዎች ከተዘጋጀ የጉብኝት፣ የግብዣ ወይም ሌላ መሰል እንቅስቃሴዎች ላይ ከመሳተፍ መታቀብ፣ ሐ) ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩን ከመደገፍ ወይም ከመንቀፍ መቆጠብ፤ ከባለስልጣናት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከእጩ ተወዳዳሪዎች ከመራጮችና ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የተያያዘ ወይም አወዛጋቢ በሆነ የምርጫ ጉዳይ ላይ ወገንተኝነትን ከማሳየት ወይም ከመግለጽ መታቀብ፣ አለባት።





መ) የማንኛውንም በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ የፖለቲካ ድርጅትን ወይም እጩን፣ ማንኛውንም አይነት ምልክት ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ በግቢዋ፣ በቢሮዋ፣ በመጓጓዣዋ፣ በራሷ ላይ እንደሁኔታው በማሳየት፣ በመያዝ፣ በማስቀመጥ፣ በመስቀል፣ በመለጠፍ ወይም በመልበስ በመሳሰለው ሁኔታ መንቀሳቀስ፣ ማሳየት ወይም ይዞ መገኘት የለባትም።

አንቀጽ **18.** <u>የምርጫን ሚስጥራዊነት እና የመራጮችን መብት ስለማክበር</u>

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ተወካዩዋ፤

ሀ) መራጩ ድምፁን ለማን እንደሰጠ ወይም ማንን እንደሚመርጥ መጠየቅ የለባትም። ለ) በምትታዘብበት ወቅት የምርጫ ሂደቱን በሚያውክ ሁኔታ የምስል እና የድምፅ መቅረጫ መሳሪያ መጠቀም የለባትም።

ሐ) መራጭ ድምፅ በሚስጢር የሚሰጥበት ክፍል ወይም ለዚሁ የተከለለ ቦታ ካሜራም ሆነ ሌላ የድምፅ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ መጠቀም የለባትም።

መ) ማንኛውንም ለመመዝገብ የቀረበች መራጭ ወይም ድምፅ ለመስጠት የተገኘች መራጭ ወይም የምርጫ አስፈፃሚ ያለፈቃዷ ወይም በግልፅ እየተቃወመች በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም በቃለ-መጠይቅ ማወያየት የለባትም ።

ሠ) የመራጮች ምዝገባ መረጃዎች በሰነድ ላይ ሲሰፍሩ ወይም መራጩ በድምፅ መስጫው ወረቀት

ላይ የምርጫ ምልክት ሲያደርግ፣ ተደብቃ በፊልም መቅረጽ ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት የለባትም።

ረ) የድምፅ ሰጪዎችን የግላዊነት መብት በሚነካ አኳኋን የመራጮችን መዝገብ፣ የመራጮችን ምዝገባ መታወቂያ ወይም ማናቸውንም ሌላ ሰነድ በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም ኮፒ ማድረግ የለባትም።





አንቀፅ **19.** <u>ጥቅም አለመቀበል ወይም አለመስጠት</u>

ማንኛውም የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ተወካይዋ ከማንኛውም በምርጫ እንቅስቃሴ ከሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅት፣ እጩ፣ ደጋፊ ወይም ማንኛውም ሰው ወይም አካል በምርጫ ሂደት ማንኛውንም ተግባር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ወይም በደጋፊነት ለመንቀሳቀስ በማሰብ ጥቅም መቀበል ወይም መስጠት፣ ለመቀበል ወይም ለመስጠት መዋዋል ወይም ቃል መግባት የተከለከለ ነው ።

አንቀፅ **20.** <u>የጥቅም ግጭት</u>

1) ማንኛውም የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ተወካይ፤

ሀ) የምርጫ ሂደትን ከመታዘብ ተግባሯ ጋር የተያያዘ የጥቅም ግጭትን ለቦርዱ ማሳወቅ አለባት። ለ) የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ወይም ሊያስከተል በሚችል በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ መሣተፍ የለባትም።

2) በምርጫ ታዛቢነት ሥራው ላይ በኑብረት፣ በገንዘብ፣ በዝምድና ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች ያጋጠማት ተወካይ ስትሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራችበት አካባቢ የምርጫ ክልል

ጽሕፈት ቤት እና ላሰማራት ድርጅት፤ድርጅቱ ሲሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራበት አካባቢ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እና ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት።

3) ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የጥቅም ግጭት አጋጥሚት ወይም እንደሚያጋጥማት በማወቋ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀረበች ሰው የታዛቢነት ሥራዋን አቁማ ቦርዱ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠባበቅ ይኖርባታል።





4) ቦርዱ በዚህ አንቀፅ መሠረት የጥቅም ግጭት ካጋጠመው ሰው ወይም ከሚመለከታት የምርጫ አስፈፃሚ ሪፖርት ሲደርሰው ጉዳዩ ነፃ፣ ቀጥተኛና ፍትሃዊ ምርጫን የማያደናቅፍ መሆኑን በራሱ በማጣራት በቦታው ላይ ሥራውን እንዲቀጥል ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከታዛቢነቱ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል። ውሳኔውንም ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

አንቀፅ **21.** <u>ሀቀኝነት/ እውነተኝነት</u>

ማንኛውም የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅትም ሆነ ድርጅቱ የሚያሰማራት ተወካይ፦ ሀ) በማንኛውም ጊዜ የምታቀርበው፣ የምታሰራጨው መረጃ ወይም ሪፖርት ሀቀኛ፣ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ግልፅና የማያሻማ መሆን አለበት።

ለ) ያቀረበችው ወይም ያሰራጨችው ሪፖርት ወይም መረጃ ተቀባይነት ባለው አሰራር የተሰበሰበ፣ የተጠናቀረ፣ የታተመ እና የተፈረመበት መሆን አለበት።

ሐ) የምታገኘው መረጃ በሚመለከተው አካል ውሳኔ ያልተሰጠበት ሆኖ ስታገኘው ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ በመረጃነት መጠቀም የለባትም።

## አንቀፅ 22. <u>ቅንነት</u>

1. ማንኛውም የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ተወካይዋ የታዛቢነት ተግባሯን በምታከናውንበት ሂደት ቅንነት የተሞላበት ስነምግባር ሊኖራት ይገባል።
2. ተወካይዋ የተጣለባትን ኃላፊነት ለመወጣት የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥማት ጉዳዩን ወዲያውኑ ለላካት ድርጅት ማቅረብ አለባት።






## አንቀፅ 23. <u>ስለምርጫው ውጤት አስቀድሞ አስተያየት መስጠት ስለመከልከሉ</u>

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ተወካይዋ፡-

1. የምርጫ ውጤት በቦርዱ በይፋ ከመገለፁ በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ሆኖ ስለምርጫው ውጤት አስተያየት መስጠት ክልክል ነው።
2. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የምርጫ ታዛቢ ድርጅቱን ስለሚወክሉት የምርጫ ታዛቢዎች ዝግጅት እና የመሳሰሉት ላይ አስቀድሞ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል።



## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

አንቀፅ **24.** <u>ፈቃድ የሚታገድበት ወይም የሚሠረዝበት ሁኔታ</u>

1. ቦርዱ አንድ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ተወካይዋ የምርጫ ሂደትን እንድትከታተል የሰጠውን ፈቃድ እንደአግባብነቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል፤

ሀ. አግባብነት ያለቸው ህጐችን ወይም የተስማማችበትን የስነ-ምግባር መመሪያ የሚጥስ ተግባር ፈፅማ ስትገኝ፣

ለ. በህግ ከተደነገገው ውጭ ማንኛውንም አድልኦ ለየትኛውም እጩ ወይም ፖለቲካ ፓርቲ አሳይታ ስትገኝ።

2. ቦርዱ የሰጠውን ፈቃድ ሲሰርዝ ወይም ሲያግድ ውሳኔውን የወሰነበትን ምክንያት በመግለጽ ለሚመለከተው ሰው ማሳወቅ አለበት።

አንቀፅ **25.** <u>ስለሚወሰድ እርምጃ</u>


የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ተወካይዋ ከዚህ የስነ-ምግባር መመሪያ እና ከገባችው ግዴታ ውጪ ስትንቀሳቀስ ከተገኘች ቦርዱ እንደሁኔታው፦

ሀ) ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቷን እንድታርም ወይም ተወካይዋ እንድትቀየር ሊያደርግ፣

ለ) ለአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም /እና ፣

ሐ) ድርጊቱ የሌሎች ህጎችን ድንጋጌዎች የሚጥስ ከሆነ በህግ እንድትጠየቅ ጉዳዩን ስልጣን ላለው አካል ሊመራው ይችላል።





አንቀፅ **26.** <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት።

አንቀፅ **27.** <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች</u>

ማንኛውም ከዚህ መመሪያ ጋር ተቃራኒ የሆነ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ

ተፈፃሚነት የለውም።

አንቀፅ **28.** *<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>*

ይህ *መመሪያ* ከየካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
ሰብሳቢ